**9** የኃይል መስመሮችን (**power strips**) የማብሪያና ማጥፊ መቀየሪያዎችን በመጠቀም ከ"ፋንቶም ኃይል" (“**Phantom Power**”) መቋረጥ ይጠበቁ። አብዛኛዎቹ የኮረንቲ መሳሪያዎች በጥቅም ላይ በማይውሉበት ጊዜ ወይም " በተጠንቀቅ" ዘዴ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ከጠቅላላ የኃይል ፍጆታቸው ላይ 75% ይጠቀማሉ። ወደ ሁሉም ወደ መሳሪያዎች የሚተላለፈውን ኃይል በአንድ ቁልፍ ለመዝጋት ቴሌቪዥኖችን ፣ የዲቪዲ ማጫዎቻችን ፣ የስልክ ኃይል መሙያዎችን (chargers) እና ሌላ አልፎ አልፎ በጥቅም ላይ የሚውሉትን መሳሪያዎች በኃይል መስመሮች ላይ ይሰኩ። እንደ መጥበሻዎች ፣ መከተፊያዎች ፣ ማቡኪያዎች ፣ የማይክሮዌቭ ምድጃዎችን የመሳሰሉትን ትናንሽ መሳሪያዎችን የመንቀል ልምድ ያኅልብቱ። በጥቅም ላይ በማይውሉበት ጊዜ ኃይል ለመቆጠብ። የሚጠብቁ የወጪ ማዳኛዎች **_5%**

*-ማጣቀሻ(www.greenamerica.com)*

**10** በመጨረሻ ፣ የቤቶችዎን ኃይል ሁኔታ ለመገምገምና የኃይልዎን ብቃት ለማሻሻል ለመርዳት ባለሞያ የኃይል አማካሪ ሙሉ የቤት ኃይል ማጣሪያ እንዲያካሄድ ያዘጋጁ። በአጠቃላይ ማጣራያው ከሁሉ በበለጠ ማሻሽያ የሚያስፈልጋቸውን አካባቢዎች ይለያል። ቤቶቻቸው ከ3,000 ካሬ ጫማ በታች የሆነ የዲ ሲ ኗሪዎች በዲ ሲ ዘላቂ የኃይል ቁሳቁስ (DC Sustainable Energy Utility) አማካይነት ነጻ የቤት ኃይል ማጣሪያ የመጠየቅ ብቃት አላቸው።

ስለ ዘላቂ የኃይል ቁሳቁስ ለማወቅ ለነጻ የቤት ኃይል ማጣሪያ
ቀጠሮ ለማስያዝ
ቀጥሎ ባለው ቁጥር ይደውሉ፤

***1-855-693-2738***

Energy Efficiency Made Simple

## የተጠቀሙ የተቀነባበረ የኃይል ብቃት ማስሊያዎች ( **interactiveenergy efficiency calculators)** ያሉበት ማገናኛዎች ፤

- የአሜሪካ የኃይል መምሪያ
  www.energy.gov/energytips.htm
- በመኪና ፣ በባቡር ወይም በአይሮፕላን የሚጓዘውን የቤተሰብዎን የካርቦን ዱካ በሚከተለው ድረ ገጽ ይዩ
  www.terrapass.com/TerraPass

ይወቁ እና ይጠንክሩ ለኃይል ቁጠባዎች ያኃይል ኃይል ያግኙ!

- አረንጓዴ አሜሪካ www.greenamerica.com
- የአሜሪካ የኃይል መምሪያ
  www.usdoe.gov

የOPCን ምክር ተቀብለው እነዚያን ኃይል ቆጣቢ የሆኑትን እርምጃዎች በቤትዎ ያካትቱ። የኃይል ቁጠባ አጥጋቢ ውጤት አግኝተው ባለታሪክ ከሆኑ ፣ የህዝብ አማካሪ ጽ/ቤት በመገናኘት የኃይል ቁጠባ እርምጃዎችን እቤታቸው ለማካተት ለሚፈልጉ ኗሪዎች እንዴት እንዳደረጉ ለምን አያካፍሉም።

የኃይል ቁጠባ ታሪኮችዎን ለማካፈል ፣ ከኃይል ቁጠባ ቆጣቢ ታሪኮችዎ ጋር ኢሜይል ለሚከተለው ያድርጉ ፤

***pnelson@opc-dc.gov.***

*OPC የኃይልና የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ደንበኞችን የሚወክል የኮሎምቢያ ድስትርክት መንግሥት ገለልተኛ ድርጅት ነው።*

**AMHARIC**

የዲ ሲ የህዝብ ጠበቃ ጽ/ቤት

# የኃይል ብቃት ( ቁጠባ) ቀላል ሆኖአል

1133 15th Street, NW, Suite 500
Washington, DC 20005
ስልክ ፤ 202.727.3071
መስማት ለተሳናቸው (TTY/TDD )፤ 202.727.2876
ፋክስ 202.727.3071
ኢሜይል፤ ccceo@opc-dc.gov
ድረ ገጽ፤ www.opc-dc.gov
Facebook.com/DCPeoplesCounsel

**1** ለወርሃዊ የማሞቂያና የማቀዝቀዣ ወጪዎች ምን ያህል እንደሚከፍሉ ይወቁ።
የኃይል ቁጠባ ለውጦችን ከማድረግዎ በፊት አማካይ ዓመታዊውን የማሞቂያና የማቀዝቀዣ አጠቃቀምና የገንዘብ መጠን ለማወቅ ከፍጆታ ቁሳቁሶች ድርጅቶች የ12 ወር የጋዝና የኃይል ደረሰኝ ያግኙ። ትክክለኛውን የኃይል ቁጠባዎችን ለማየት ከዚያም የኃይል ቁጠባ ማሻሸያዎችን ካደረጉ በኋላ በወጪዎችዎ መካከል ያለውን ልዩነት ያስሉ።

**2.** ለቤተሰብ ጉዳይ ሲወጡ መብራት እንዲጠፋ ያድርጉ።

ፈጣሪ ይሆኑ እና በማብሪያ-ማጥፊያ ላይ ማስታወሻዎችን ልጆች ይለጥፉ ዘንድ ያሳትፉአቸው። ደግሞ ፣ ከክፍል ስወጡ ወይም ወደ ክፍል ስገቡ በራሱ የሚያጠፋውንና የሚያበራውን ማብሪያና ማጥፊያ ለመትካል ያስቡ።
ይህ ቀላል የባህርይ ለውጥ *2%* የኃይል ቁጠባ ሊያስከትል ይችላል።
2 ማጣቀሻ ፤ *([www.greenamerica.com](http://www.greenamerica.com))*

**3** የውስጥና የውጭ አምፑሎችዎን ( ተገቢ ከሆነ ) በcompact Fluorescent Light Bulbs (CFLs) ወይም Light-Emitting Diodes (LEDs) ይተኩ። እነዚህ አምፑሎች ከመደበኛ incandescent አምፑሎች የበለጠ ውድ ሲሆኑ፣ እነዚያ የበለጠውን ኃይል ቆጣቢና በረጅም ጊዜ ውስጥ ወጪ ይቀንሳሉ። እቤትዎና በቤትዎ አካባቢ ያሉትን አምፑሎች መቀየር ከኃይል ወጭዎችዎ ላይ *10%* ሊቀንስ ይችላል።
ማጣቀሻ ፤ *([www.usdoe.gov](http://www.usdoe.gov))*



**4** እቤትዎ ከሁሉ እጅግ በሚጠቀሙአቸው ክፍሎች ውስጥ በማቀዝቀዣ ወራት ውስጥ ምቾት እየሰጠዎት ለአየር ማቀዝቀዣዎችዎ ዕረፍት ለመስጠት የኃይል ኮከብ （ENERGY STAR） እንደሆኑ ማዕረግ የተሰጣቸውን የጣሪያ ማረገቢያዎችን ይትከሉ። በማሞቂያ ወራት ውስጥ የጣሪያ ማረገቢያዎችን ከቀኝ ወደ ግራ ማዞር ሞቃት አየር እቤትዎ ውስጥ እንዲዘዋወር ዘንድ ይረዳል።
ENERGY STAR ብቃት ባላቸው ምርቶችና ሂደቶች አማካይነት ሁላችንም ገንዘብ እንድንቆጥብና አካባቢን እንድንከላከል ለመርዳት የአሜሪካ የአካባቢ ጥበቃ ድርጅትና የአሜሪካ የኃይል መምሪያ ጥምር መርሃ ግብር ነው። ስለ ***Energy Star*** የበለጠውን ለማወው ወደ ***www.doe.gov*** ይሂዱ። የሚጠብቁ የወጪ ማዳኛዎች ***_19%***

ማጣቀሻ ፤ ([www.greenamerica.com](http://www.greenamerica.com))

5. ማቀዝቀዣዎችዎን አይርሱ። በተላይ ቤትዎ እ ኤ አ ከ1993 ዓ ም በፊት ተሰርቶ ከሆነ ከሁሉ እጅግ በበለጠ ታላላቅ የኃይል “ጫላጮች” መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል። በቀላሉ ከመሳሪያ በስተጀርባ ያሉትን የማቀዝቀዣ ሽቦችዎችን በየስድስት ወር መጥረግ በአጥጋቢ ሁኔታ እንዲሠራ ያደርገዋል። ሌላ ጠቃሚ ጥቆማ ይኸውና ፤ ሙሉ ማቀዝቀዣ ትንሽ ኃይል ይጠቀማል። ቀዝቃዛ ቴምፔሬቹር ለመጠበቅ ለመርዳት ጥቅም ላይ ያልዋለውን ቦታ ለመሙላት በጀርካን ውኃ ሞልተው ያስቀምጡ። ሁለተኛ ማቀዝቀዣ ካሉዎት ፣ ያስወግዱት ወይም ይንቀሉት።
5 የሚጠብቁ የወጪ ማዳኛዎች _ ***4%***

ማጣቀሻ ፤ *([www.greenamerica.com](http://www.greenamerica.com))*

**6**. ማጠቢያዎችና ማድረቂያዎች – ልብሶችዎን በቀዝቃዛ ውኃ ማጠብ ውኃ ሙቅ እንደሚያጸዳ ያህል አጽድቶ የማጠቢያዎችን ኃይል በግማሽ እንደሚቀንስ ያውቁ ኖሮአል? እንደዚያውም ልብሶችዎን እቤት ውስጥ ወይም ከቤት ውጭ ባለው ማንጠልጠያ አስጥቶ ማድረቅ ዓመታዊ የኃይል ወጪዎን በ$100 ይቀንሳል።

ማጠቢያዎንና ማድረቂያዎን ለመተካት እያቀዱ ከሆነ ፣ በኃይል ኮከብ እንደሆኑ ማዕረግ የተሰጣቸውን መሳሪያዎች ይቀይሩ። የኮሎምቢያ ድስትርክት ዘላቂ ኃይል መሠረታዊ አገልግሎቶች (DC SEU) በኃይል ብቃትና በሚታደሱ የኃይል መርሃ ግብሮች አማካይነት የድስትርክቱን ቤተሰቦችና ተቋሞች ኃይልና ገንዘብ ለመቆጠብ ለመርዳት የታቀደ ነው። ስለ መርሃ ግብሮችና የዋጋ ቅናሾች በተመለከተ በ DC SEU ድረ ሞገድ በ www.http://www.dcseu.com ይገኛል።
የሚጠብቁ የወጪ ማዳኛዎች **_ 12%**
ማጣቀሻ ፤ *([www.greenamerica.com](http://www.greenamerica.com))*

**7** በበሮችና በመስኮቶችዎ አካባቢ የሚገኘውን ቀዳዳ ሰም በመሰለ ነገር መድፈንና ለአየር ሁኔታ በሚመች ሁኔታ መለጣጠፍ አዲስ መስኮት ከመቀየር ይልቅ ዘወትር ወጪ ቆጣቢ ነው። በመስኮቶች ላይ ሙቃት ወይም ቅዝቃዜ የሚያግዱ መጋረጃዎችን ለማድረግ ያስቡ ፣ በመስኮቶች መስተዋት ላይ በዝቅተኛ ሁኔታ አስተላላፊ (low-emissivity (low-e) ጨርቅ ማድረግ እና በተጨማሪ በክረምት ሞቃትና በበጋ ቅዝቃዜ ለመጠበቅ የንፋስ መስኮቶችን ወይም የላስቲክ መስኮት መለበጃዎችን ማድረግ።
የሚጠብቁ የወጪ ማዳኛዎች **_ 12%**
-ማጠቀሻዎች *([www.greeamerica.com](http://www.greeamerica.com))*

**8** የማሞቂያና የማቀዝቀዣ ቁሳቁሶችዎን በመለው ዓመት ውስጥ ብቃት ባለው ሁኔታ ለመቆጣጠር ፕሮግራም የሚደረግባት (መስተካከል የሚችል )ቴርሞእስታት (programmable thermostat) ይግጠሙ። ፕሮግራም የሚደረግባት ቴርሞእስታት ቀድሞውኑ ካሉዎት ፣ በተገቢ ሰዓቶች የሚገኘውን የሞቃት ወይም የቅዝቃዜ መጠን ለማስተካከል የተሰተካከለ መሆኑን ለማረጋገጥ በየጥቂት ወራት ውስጥ ይዩ። ለምሳሌ ፣ እርስዎ በሚተኙበት ወይም በስራ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ፣ የኃይል ብቃት እጅግ ከፍ ለማድረግ የሞቃት ወይም የቅዝቃዜ መጠን ለማስተካከል በሚችል ሁኔታ የተስተካከለ ነው? መርሃ ግብርዎ ቢቀየር ፣ የቴርሞእስታት አሠራሮችዎን በማስተካከል የበለጠውን ወጪ እንዴት ሊቀንሱ ይችላሉ?
የሚጠብቁ የወጪ ማዳኛዎች **_ 10%**
-ማጣቀሻ*(www.greenamerica.com)*